በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአክሱም ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የአክሱም ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደብዳቤ ቁጥር Axum/5828/05/09 በቀን 29/12/2009 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በዩኒቨርሲቲው የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

<u>**ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣**</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. ዩኒቨርሲቲው በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበስባቸው ገቢዎች የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

   - ከ23 ንግድ ቤቶች ከ1 አመት በላይ ሳይሰበሰብ የቆየ ውዝፍ ኪራይ በ2008 በጀት አመት ብር 236,040.00 እና በ2009 በጀት አመት ብር 257,147.94 በድምሩ ብር 493,187.94 ያልተሰበሰበ የኪራይ ሂሳብና ውሉ ላይ 15% በተቀመጠው መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ሂሳብ ብር 73,978.19 በጠቅላላው ብር 567,166.13 በውዝፍ የሚገኝ መሆኑ፤
   - ከተጠቀሱት ንግድ ቤቶች (እነመብሪሂትና ትርሃስ፤ እነ አጸደአለም፤ ቴዎድሮስ ካህሳይ) ከተቋሙ ጋር የገቡት ውለታ ከሰነዳቸው ጋር ያልተገኘ መሆኑ፤
   - በበጀት ዓመቱ በናሙና ከተመረጡት የዱቤ ተጠቃሚዎች መሰብሰብ ከነበረበት ውስጥ ብር 4,844.82 ያልተሰበሰበ መሆኑ

2. በዋናው ግቢ የመኖርያ ቤት ላገኙ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የሚከፈላቸው የቤት አበል ሙሉ በሙሉ መቆም /መቋረጥ/ ሲገባው፣ የመንግስት የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በድጋሚ ብር 575,690.40 ተከፍሎ መገኘቱ፣

3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀፅ 5 ተራ ቁጥር 2/ሀ በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሊታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የወጣው ወጪ በቦርድ መፈቀድ እንዳለበት

   አንቀፅ 3 የፋይናንስ አስተዳደር በሚለው ስር ‹‹የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን ጥቅም ላይ ማዋል የሚችሉት ፀንተው በሚሰራባቸው ህጎችና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ እንደሆነ›› መመሪያው ከማመልከቱም በተጨማሪ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር ት/ሚ.259/52-18/03 ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ፣

   - ለተለያዩ የት/ት ክፍል መምህራን የክረምትና የማታ ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ኮርስ ላስተማሩበት ለረዳት ፕሮፌሰር ብር 120.00 የነበረውን ብር 180.00፣ ለሌክቸረር ብር 100.00 የነበውን ብር 160.00፣ ለረዳት ሌክቸረር ብር 65.00 የነበረውን ብር 85.00 በማድረግ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,472,773.20 የተከፈለ መሆኑ
   - ለአስተዳደር ሰራተኞች ለሬጅስትራርና አልሙናይ ዳይሬክቶሬት እና ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ብር 97,021.66 የተከፈለ መሆኑ
   - በኤክስቴንሽን መርሃ ግብር በመጀመሪያ ድግሪ፣ ለሁለተኛ ድግሪ፣ ትምህርታቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች፣በተለያዩ ኮሌጆችና የት/ት ክፍሎች ላስተባበሩ ሰራተኞች የፖዚሽን ክፍያ፣ ለት/ት ክፍል ሃላፊዎች ለአስተባባሪዎች የተከፈለ ብር 2,784,095.00 የተከፈለ መሆኑ፣

   በድምሩ ብር 4,353,889.86 በቦርድ ሳይፈቀድ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑ፣

4. ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ

የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር፡

- ዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ጽሑፍ ያማከሩበት በሚል በአንድ ተማሪ ብር 5,000፣ ብር 2,000፣ በማድረግ በድምሩ ብር 200,000.00፤
- ለኢንተርናል ኤግዛማይነር (የውስጥ ገምጋሚ) በአንድ ተማሪ ብር 2,500፣ በማድረግ በድምሩ ብር 162,500፤
- ለኤክስተርናል ኤግዛማይነር (የውጭ ገምጋሚ) በአንድ ተማሪ ብር 4,000፣ በማድረግ በድምሩ ብር 184,000.00፤
- ለቼር ፐርሰን (ሰብሳቢ) በአንድ ተማሪ ብር 200፣ በማድረግ ብር 13,800.00፤

በኦዲት ናሙና በተመረጡት ብቻ በአጠቃላይ ብር 560,300.00 በመንግስት የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተከፈለ መሆኑ፤

5. በዩኒቨርሲቲ የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ36 የውጭ ሀገር መምህራን ብር 2,707,460.71 የተከፈላቸው ቢሆንም የሥራ ግብር ብር 882,559.14 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ፤
6. ለማስተርስ ድግሪ ከሃያ አራት ወር (2 ዓመት) ለዶክትሬት ድግሪ ከአራት ዓመት መብለጥ እንደሌለበትና ከበለጠ ግን እድሉን የሰጠው ተቋም ማረጋገጥ እንዳለበት›› መመሪያው ቢያመለክትም ዩኒቨርሲቲው ውል ገብተው ለሁለተኛ ዲግሪ 9 ለሦስተኛ ዲግሪ 3 በድምሩ 12 ከሀገር ወጭ ትምህርታቸው ከሚከታተሉ መምህራን መካከል ከላይ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያለፈ ሲሆን አካዳሚክ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ሳይቀርብ በበጀት ዓመቱ ብር 994,941.00 ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
7. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ አቅራቢዎች ለዘገዩበት ጊዜ መቀጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡
   - የህንፃ ስራው ለዘገየበት በ4 የስራ ተቋራጮች ከሚሰሩት ከ4 ፕሮጀክቶች ላይ መሰብሰብ የነበረበት የጉዳት ካሳ ብር 7,347,911.16 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- ከተለያዩ የእቃ አቅራቢዎች በወቅቱ እቃውን ገቢ ባለማድረጋቸው ብር 138,234.13 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

በጠቅላላው ብር 7,486,145.29 መክፈል የሚገባቸው የጉዳት ካሳ ያልከፈሉ መሆኑ፤

8. የመንግሥት መ/ቤት ከአቅራቢዎች እና በውሉ መሠረት የተያዘ ዋስትናዎች፤ ዋራንቲዎች ተገቢውን ክትትል እየተደረገባቸው አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ እንዲሰጥባቸው መመሪያው ቢያመለክትም፤ የነጭ ጤፍ አቅራቢ ከሆነ ሮማን ከበደው ከ01/09/2009 ጀምሮ 5000 ኩንታል ጤፍ እንዲያቀርብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሠረት ባለማቅረቡ ያስያዙት ዋስትና ብር 1,049,500.00 ተወርሶ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረግ ሲገባው ዩኒቨርስቲው በ 22/03/2010 ዓ.ም ለባንኩ በፃፈው ደብዳቤ ያስያዙት ቦንድ እንዲታገድ ብቻ የጠየቀ መሆኑ፤
9. በጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል የመንግስትን ወጪ ሊቀንስ በሚችል መልኩ የግዥ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ አውጥቶ በርካታ ድርጅቶችን በማሳተፍ የመንግስት ጥቅም ማስጠበቅ ሲገባ፣ በናሙና ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ፣ ግዥን በመቆራረጥ የተከናወኑ ክፍያዎች ብር 1,177,071.33 መፈፀሙ፤
10. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ለ2008-2010 የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ለዩኒቨርሲቲው በላከው ውል ላይ የአንዱ Brother Toner TN3320 የንግድ ምልክት ADDIS TONER ሞዴል TN720/TN3330/TN3310/TN3320 ዋጋ ከነቫቱ ብር 661.25 ከቪር ጀነራል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ አቅራቢ ጋር ውል ያሰረ ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲው ከፈጸማቸው ግዥዎች ውስጥ የተገለጸው ተመሳሳይ እቃና ሞዴል በቁጥር 60 ከብሪጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ በዋጋ ማወዳደሪያ ያንዱ ዋጋ ከነቫቱ ብር 2,050.01 ከማእቀፍ ግዥ ስምምነት ውጪ ግዥ በመፈጸሙ (60*2,050.01) =123,000.09 — (60*661.25) = 39,675.00 በአጠቃላይ ብር 83,325.09 አለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
11. ዓባይ ኮንሰልቲንግ ኮንስትራሽንና ኢንጂነሪንግ ለአማካሪነት እና ሱፐርቫይዘርነት ክፍያ በ2008 በጀት ዓመት መከፈል የሚገባው ብር 638,250.00 ከበጀት ዓመቱ ውጪ በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

12. በተቋሙ የኤሌክትሪክ ኃይል ግምት EEU-NORTHEN REGIONን 796.4 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ሥራን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የግምት ሂሳብ ብር 1,804,956.36 እንደሆነና የዋጋ ልዩነት ቢከሰት ልዩነቱን ተቋሙ እንደሚከፍል ተገልፆ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን የመስመር ዝርጋታው ስለመጠናቀቁ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብና አገልግሎቱ ሳይገኝ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

13. በዋናው ግቢ ቴዎድሮስ አበራ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር ለአስተዳደር ሕንፃ /Administration office building (Lot 24) ለማሰራት በዋናው ውል ብር 88,482,547.44 ለተለዋጭ ሥራ /variation Order/ ብር 1,134,144.46 በድምሩ በብር 89,616,691.90 ለመስራት ተዋውሎ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 22,602,258.11 የተከፈለው ሲሆን ከተቋሙ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተረጋግጦ በተሰጠን ማስረጃ ሥራው የደረሰበት ደረጃ 28.07% መሆኑና ከቀን 01/03/09 ዓ.ም ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር AKU/VPASA 4483/01/09 የሥራ ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን ያቋረጠ ቢሆንም በውሉ መሠረት በሕግ የተጠየቀበት እና ውሳኔ የተገኘበት ማስረጃ የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንፃር በሥራ ተቋራጩ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

14. ከኢፌዴሪ ት/ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር 7/-259/1715//09 በቀን17/02/09 በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተባባሪነት የዩኒቨርሲቲዎችን ኔትወርክ ዝርጋታ የሁሉንም ተቋማት ፍላጎት አቀናጅቶ ለመስራት ለሁሉም ፕሮጀክቶች መሣሪያዎች ከውጪ የሚመጡ መሆናቸውን በመጥቀስ የተቋሙን ድርሻ ወደ ት/ሚ/ የባንክ ሂሳብ እንዲያስተላልፍ የገለፀ ቢሆንም፤ መሣሪያዎች ግዥ ተፈፅሞ ስለመግባታቸው እና ርክክብ ስለመፈፀሙ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው፤ የመሠረተ-ልማት የኔትወርክ ዝርጋታው በአግባቡ ስለመፈፀሙ የግንባታ የክፍያ ምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲስ ሳይፀድቅ እና አገልግሎት መስጠቱ ሳይረጋገጥ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 468205 በቀን 30/10/09 ብር 51,000,000.00 ክፍያው ተፈፅሞ እና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

15. **የተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ፤**

- በሂሣብ መደብ 4203 ለ99 ግለሰቦች በቅድሚያ የተከፈለ ብር 730,447.75 ሂሳቡ ሳይወራረድ ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ድረስ የቆየ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ በዚሁ ሂሳብ መደብ ለ5 ግለሰቦች እና ድርጅቶች በቅድሚያ የተከፈለ ብር 45,990.00

ሂሳቡ ሳይወራረድ ከ4 ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ፤ በድምሩ ብር 776,437.75 መኖሩ፤

- በበሂሣብ መደብ 4251 በተቋሙ ዋናው ግቢ ቴዎድሮስ አበራ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር ለአስተዳደር ሕንፃ /Administration office building (Lot 24) ለማሰራት ተዋውሎ በቅድመ ክፍያ የተከፈለ ቢሆንም የሕንፃ ሥራው ተቋርጦ የሚገኝ እና በህንፃ ተቋራጩ ስም የሚገኝ በወቅቱ ያልተወራረደ እና ከ1 ዓመት ከ4ወር በላይ የቆየ ብር 19,946,833.32 የሚገኝ መሆኑ፤
- በ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት (ከ30/07/2007 እስከ 30/5/2009) ባለው ጊዜ ውስጥ ጂ .አይ .ዜድ.አይ.ኤስ ቸ /GIZI-IS/ ራሱ እና ከሌሎች 3 የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ጋር በመሆን ለአቅራቢዎች በሚሰጥ የቅድመ-ክፍያ ብር-10,097,839.44 ከ10 ወር እስከ 2-ዓመት ከ9 ወር የቆየ ሂሳብ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡በጠቅላለው ብር 50,970,328.30 ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ የቆየ የተሰብሳቢ ሂሣብ መኖሩ፤

16 የተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ከመደበኛ ብር 5,485,644.85 ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ከ4 ወር ከውስጥ ገቢ ደግሞ ብር 2,347,612.12 ፤ በድምሩ ብር 7,833,256.97 በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል መገኘቱ፤

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ሪፈራል ሆስፒታል በገንዘብ የገቢ ማጠቃለያ /በሞዴል 64/ ቁጥር 117651 ከ23/09/09 እስከ 05/10/09 የተሰበሰበው ገቢ ብር 14,190.10

ወደ ባንክ በቀን 11/10/09 ዓ.ም ከ6 ቀን እስከ 18 ቀናት በማዘግየት ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግ መሆኑ፤

❖ ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ እንደሆነ መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በዋናው ገቢ፤ ከሞኤንኮ (የኢትዮጵያ የሞተርና የመሀንዲስነት ማህበር ሊሚትድ አ.ማ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ለተገዛበት ብር 612,831.88፤ ሲከፈል መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ (cash sale invoice) መሆን ሲገባው፣ ሂሳቡ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (Cerdit sale invoice) በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

❖ በ2009 በጀት ዓመት ርክክብ ተፈጽሞባቸው በከፊል አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ በ2 ሎት የተከፈሉ ጠቅላላ ዋጋ በድምሩ ብር **352,703,934.88** ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር **345,258,961.91** ወጪ የተደረገባቸው ሕንፃዎች መሰረተ ልማት ባለመሟላቱ ሙሉ የሆነ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

<u>ሌሎች ጉዳዮች</u>

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

<u>የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በሽሬ ካምፓስ

<u>የንብረት ክምችትን በተመለከተ</u>

- በንብረት ክፍል ከ1 ዓመት በፊት ተገዝተው ያለአገልግሎት የተለያዩ ብረት ድስቶች የተለያየ መጠን እና ይዘት ያላቸው፤ white board ተከማችተው ያሉ መሆኑ፤
- የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ከሌሎች ቋሚና አላቂ ንብረቶች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ብዛት ያላቸው የኮምፒውተር ወረቀቶች፤

- ብዛት ያላቸው ፍሊቶች ከ1 ዓመት በላይ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

<u>**ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች**</u>

- ብዛት ያላቸው ማይክሮስኮፖች /የላቦራቶሪ ዕቃዎች/
- ዴል ላፕቶፖች
- ለሥነ ምድር ጥናት የሚያገለግል መሣሪያ እና ፍሪጆች፣ የሽንኩርት መፍጫ፣ የምግብ ማብሰያ ማሽኖች ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘቱ፤
- የቤተ-መጽሐፍት ንብረት ቆጠራ እና የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች በዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ውስጥ እንዳልተካተቱ፤
- በጤና ሳይንስና ሪፈራል ሆስፒታል በተካሄደው የንብረት ቆጠራ በሰራተኞች እጅ የሚገኙ 13 ላፕቶፖች በሰኔ 30/2009 በቆጠራ ያልተካተቱ መሆኑ፤

ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢው ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ላፕቶፕና አድቫንስ ባልመለሱና ክስ ከተመሰረተባቸው ብር 79,373.30 የገንዘብ መጠን የያዙ 5 ጉዳዮች እስካሁን ገንዘቡ ከባለጉዳዮቹ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ውስጥ ብር 8,200.00 ቪዲዮ ካሜራ ያልመለሰና በክርክር ሂደት ያለ መሆኑ፤
- የውል ግዴታቸውን ባልተወጡ ላይ በህግ ክፍል ክስ መመስረት ሲገባው ያልተመሰረተባቸው 8 ባለጉዳዮች የሚፈለግ ብር 354,628.22 በኦዲት ወቅት የተገኘ መሆኑ፤

እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣

- የትርፍ ሰአት ላስተማሩ መምህራን፣ ከመሰናዶ ት/ቤቶች የተውጣጡ ተማሪዎችን (out Reach) ላስተማሩ የተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን እና የክረምት ትምህርት ላስተማሩ መምህራን በክሬዲት አወር (credit hours) እንዲከፈል ከተፈቀደው መጠን በላይ በድምሩ ብር 1,198,264.48 ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለ፣

- ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በአይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ብር 31,200.00 በቀጥታ እና ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ኪራይ ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ ብር 262,275.00፣ በድምሩ ብር 293,475.00 በዓይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ያለአግባብ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ ይህ ግኝት በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት አስተ በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ሳይወሰን ወይም ሌላ በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር የተፈፀመ፤
- በዩኒቨርሲቲው ማናጅሜንት ካውንስል በተወሰነው መሠረት ከባንክ ወጪ ሆኖ ብር 5,269,247.42 ለተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ሞጁል ላዘጋጁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ፣ ፈተና ለፈተኑ እና ላማከሩ በሚል በድምሩ ብር 696,583.32 የተከፈለ መሆኑ ፣
- የመጀመሪያ እና የ2ኛ ዲግሪ፣ የክረምት ት/ት እንዲሁም የኤክስቴሽን ት/ት ላስተባበሩበት የፖዚሽን /Overload/ ክፍያ በሚል ለተለያዩ የአስተዳደርና የአካደሚክ ሠራተኞች ብር 2,115,860.00 የተከፈለ፣በድምሩ ብር 8,081,690.74 በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ መወሰን ያለበት ክፍያ ሳይወሰን ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንምበ2009 በጀት ዓመትም በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

9.1.3 <u>የዕቃና የአገልግሎት ግዥ፣</u>

- ብር 906,468.95 በተራ ፋክቱር ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡-
- ብር 324,962.22 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ሂሳቡ ተወራርዶ መገኘቱ፡-
- ብር 187,484.07 ገንዘቡ መከፈሉን የሚያረጋግጥ የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (credit sales invoice) ብቻ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፡-
- ብር 18,440,235.40 ከገቡበት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች መሰብሰብ የነበረበት የጉዳት ካሳ አለመሰብሰቡ፣
- ከ2008-2010 የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ለዩኒቨርሲቲው በላከው ውል ላይ የአንድ UPS 1500VA የንግድ ምልክት BPC ሞዴል Powergempro1500ES ዋጋ

ከነባቱ ብር 10,079.75 መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ግዥ ሲፈጸም ያንዱ ዋጋ ብር 12,989.25 በሆነ ዋጋ በመገዛቱበድምሩብር 203,665.00 (/70*12,989.25/-/70*10,079.75/) ለአቅራቢ ድርጅቱ በብልጫ መከፈሉ፣እና ተመላሽ አለመደረጉ፤-

ነዳጅን በተመለከተ

- ስለዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ አጠቃቀምም ሆነ በዩኒቨርሲቲው ሥር ስላሉት ተሽከርካሪዎች መረጃ በመመሪያው በተቀመጠው መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፣
- በዋና ግቢ፤ በሪፌራል ሆስፒታል እና በሽሬ ካምፓስ የሚገኙ፣ ባጠቃላይ የ3 ጀኔሬተሮች የነዳጅ ፍጆታ ሲዳሰስ ለጀኔሬተሮቹ የዋለውን የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ መሆኑ፣

በ2007 በጀት አመት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

- የትርፍ ሰአት ላስተማሩት የህክምና ዘርፍ ረዳት ፕሮፌሰሮች በክሬዲት አወር (credit hours) ብር 120.00 መከፈል ሲገባ ብር 400.00 በመከፈሉ ከተፈቀደው መጠን በላይ በድምሩ ብር 77,840.00 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
- በዩኒቨርሲቲው የመንግስት የጋራ መኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በየደረጃው ከሚገባቸው የቤት አበል ላይ ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ ብር 138,205.00 በዓይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ያለአግባብ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ፣
- በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የተደረገ በቁጥር አንድ ሳውንድ ፕሩፍ ጀኔሬተር ብር 4,499,700.00 የተከፈለበት ቢሆንም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች እንደገና በረጋገጡት መሰረት ዕቃው በውሉ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (specification) መሰረት አለመሆኑ ስለተረጋገጠ ዩኒቨርስቲው ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ በ2007 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት ባሉት የበጀት ዓመታት ርክክብ የተፈፀመባቸው ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

- ግንባታዎችን ውል ከገቡበት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች መሰብሰብ የነበረበት ብር 21,163,962.31 የጉዳት ካሳ አለመሰብሰቡ፣
- በፕሣ 9 የሥራ ደረጃዎች ላይ ያለውድድር እና የሥራ ልምዳቸው አግባብነት ሳይኖረው በመማር ማስተማር ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በአይ ቲ ዳይሬክተርነት እና በተቋማዊ ዕቅድና አፈፃፀም ግምገማ ማዕከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት መመደባቸው፣
- በዋናው ግቢ ቤተ-መጽሐፍት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ እንዲሁም የተገነጣጠሉና ተገቢውን ጥገና ያላገኙ የተለያዩ መጻህፍት መኖራቸው፣ በተጨማሪም በስጦታ የተገኙ ነገር ግን ዋጋቸው ያልተገለጸ የተለያዩ መጽሐፍት መኖራቸው ታውቋል፡፡

<u>የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአክሱም ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በአክሱም ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአክሱም ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሳብ</u>

1.1. 1 <u>የተሰበሰበው ገንዘብ በየዕለቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ ስለመሆኑ፤</u>

1.1.2 <u>ግኝት፤</u>

የፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 3 ተራ.ቁ. 2 ከማንኛውም የገቢ ምንጭ የሚገኝ የመንግሥት ገቢ በሕግ በተደነገገው መሠረት ተሰብስቦ በዕለቱ ወይም በማግስቱ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ የባንክ ሂሳብ መግባት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ ገቢ መደረግ ባለበት ጊዜ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ-በጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ረፈራል ሆስፒታል በገንዘብ የገቢ ማጠቃለያ /በሞዴል 64/ ቁጥር 117651 ከ23/09/09 እስከ 05/10/09 የተሰበሰበው ገቢ ብር 14,190.10 ወደ ባንክ በቀን 11/10/09 ዓ.ም ከ6 ቀን እስከ 18 ቀናት በማዘግየት ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.1.3 <u>ስጋት፡-</u>

ተቋሙ በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ የማያደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነትና፣ ለምዝበራ ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.1.4 የማሻሻያሀሳብ

በተቋሙ በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገቢ በመመሪያው በተቀመጠበት ጊዜ ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግበትን አስራር ሊዘረጋ ይገባል ማኔጅመንቱም ጥብቅ የሆነ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበውን ገንዘብ በየቀኑ ከ RV ወደ ሞዴል 64 ለማጠቃለል ካለው የሥራ ጫናና የሠራተኛ እጥረት ምክንያት በየዕለቱ ባንክ ገቢ ሊደረግ ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን በመግለፅ በቀጣይ የሚስተካከል መሆኑን ገልፀዋል፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1.1 ያልተሰበሰበ ገቢ

2.1.2 ግኝት

ዩኒቨርሲቲው በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበስባቸው ገቢዎች የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ከ23 ንግድ ቤቶች ከ2008 በጀት አመት ያልተሰበሰበ ብር 236,040.00 እና በ2009 በጀት አመት ብር 257,147.94 በድምሩ ብር 493,187.94 ውዝፍ የኪራይ ሂሳብና ውሉ ላይ 15% በተቀመጠው መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ሂሳብ ብር 73,978.19 በጠቅላላው ብር 567,166.13 ከ1 አመት በላይ ሳይሰበሰብ በውዝፍ የሚገኝ መሆኑ፤
- ከተጠቀሱት ንግድ ቤቶች (እነመብ ሪሂትና ትርሃስ፤ እነ አጸደአለም፤ ቴዎድሮስ ካህሳይ) ከተቋሙ ጋር የገቡት ውለታ ከሰነዳቸው ጋር ያልተገኘ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ በናሙና ከተመረጡት የዱቤ ተጠቃሚዎች መሰብሰብ ከነበረበት ውስጥ ብር 4,844.82 ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል

2.1.3. <u>ስጋት፤</u>

- በውሉ መሠረት መሰብሰብ የሚገባው የዱቤ ሂሳብ እና የኪራይ ገቢ ሂሳብ በወቅቱ አለመሰብሰቡ መንግስት በዕቅድ በያዛቸው ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡
- ውሉ መሰረት እርምጃ አለመውሰድ ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ መንገድ የሚከፍት አሰራር ነው፡፡

2.1.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ሆስፒታሉ በተገቢው ውለታ በውሉ መሠረት ከህክምና ከኪራይ አገልግሎት የሚገኘውን ገቢ በወቅቱ ያልሰበሰበበት ምክንያት ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.1.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በግቢው ውስጥ ያሉ ንግድ ቤቶች ያለውን የስራ አጥነት ችግር ለመፍታት በማህበር ለተደራጁ ወጣቶች የተሰጠ መሆኑን እነዚህ ወጣቶች 2 ዓመት ካደረጉ በኋላ ሌሎች ወጣቶችን ለማስገባት ከግቢ እንዲወጡ ሲጠየቁ አልተደራጀንም ብድራችን አልመለስንም በማለት ለመውጣት ፍቃደኞች በማይሆኑበት ጊዜ እነሱን ለማስወጣት በሚደረግ ጭቅጭቅ የቤት ኪራዩ በክርክር ጊዜ ያልሰራንበት ስለሆነ አንከፍልም በማለት ያልከፈሉት ሲሆን በህግ ሂደት ከ 23 ንግድ ቤቶች ከነበረው ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 280,550.00 ተመላሽ ተደርጓል የቀረውን ለማስመለስ አደጋች መሆኑን ግንዛቤ ቢወሰድበት በማለት ውላቸው ያልተያያዘውን አግኝተው ማያያዛቸውን፤
- የዱቤ ህክምና ያልተሰበሰበ የነበረው አብዛኛው ተሰብስቦ ብር 4,900.00 ቀርቷል ይህም በሚቀጥለው ይሰበሰባል። በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1.1 **ደመወዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በተመለከተ፤**

3.1.2 **አላግባብ የተፈፀመ የቤት አበልን በተመለከተ**

3.1.3 **ግኝት**

የት/ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር አካላትና የአካዳሚክ ባለሙያዎች የሚከፈሉ ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ እንዲሻሻል ባቀረበው ጥናት መሰረት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት በቀን 06/01/06 በቁጥር መ/90-1013/2 በተፃፈ ደብዳቤ ለአካዳሚክ ባለሙያዎች የቤት አበል ከመስከረም 06/2006 ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ፤ ‹‹ለፕሬዚደንት ብር 2,500.00፤ ለም/ፕሬዚደንቶች ብር 2,000.00፤ ለረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ ብር 1,000 ረዳት ሌክቸረርና ሌክቸረር ብር 800 እና ረዳት ምሩቅ I እና II ብር 600›› እንዲከፈል መወሰኑን የትምህርት ሚኒስቴር በ14/01/06 በቁጥር 7/ጠ-259/172/06 ባሳወቀው መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዋናው ግቢ

የመኖርያ ቤት ላገኙ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የሚከፈላቸው የቤት አበል ሙሉ በሙሉ መቆም /መቋረጥ/ ሲገባው፤ የመንግስት የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በድጋሚ ብር 575,690.40 ተከፍሎ መገኘቱ፤

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል

3.1.4 **ስጋት**

ከመመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ ድርጊቱም ተጠያቂነትን ያስከትላላል፡፡

3.1.5 **የማሻሻያ ሀሳብ**

የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን የሚከፈለው የቤት አበል እንዲሁም ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በድጋሚ የሚከፈለው የቤት አበል በአስቸኳይ እንዲቆም፤ አላግባብ የተከፈለውም የቤት አበል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የአካዳሚክ ባለሙያዎች ተመላሽ እንዲደረግ፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መስራት ይኖርበታል፡፡

3.1.6 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ቤትና የቤት አበል ሁለቱም በአንድ ላይ በነጻ አልሰጠንም። ይህ መስተካከል አለበት። መንግስት የፈቀደዉ የቤት አበል ከፍለናል። ዩኒቨርሲቲዉ የገዛዉ የኮንደሚንየም ቤት ለመምህር ብቻ ሳይሆን ለዩኒቨሲቲዉ ማህበረሰብ የቤት አበል ያለውም ይሁን የሌለው ከቤቱ ስታንዳርድ በመነሳት ተመን በማውጣት በኪራይ እያከራየን ነበርን ሀቁ ይህ መሆኑን ብንገባባ። ግኝቱ መምህሩ የቤት አበል ስለሚከፈለው የመንግስት ቤት መከራየት አይችልም የሚል ነው ይህም ለመምህር ነግረን አንዱን እንዲይዝ አድርገነዋል ተስተካክሏል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

3.1.7 የኦዲተር አስተያየት

ዩኒቨርሲቲው ቤቶቹን ለመግዛት ሲያስብ የትምህርት ማስተማሩ እንዳይስተጓጎል ታስቦ የተደረገ በመሆኑ በመጀመሪያ የመምህራኖቹን ጥቅም ማስጠበቁ ተገቢነት ያለው ቢሆንም የመንግስት ተጠቃሚነት በሚያሳጣ መልኩ መፈፀሙ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም አላግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.1 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ

3.2.2 ግኝት፡-

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀፅ 5 ተራ ቁጥር 2/ሀ በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሊታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የወጣው ወጪ በቦርድ መፈቀድ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት ለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለተለያዩ የት/ት ክፍል መምህራን የክረምትና የማታ ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ኮርስ ላስተማሩበት ለረዳት ፕሮፌሰር ብር 120.00 የነበረውን ብር 180.00፤ ለሌክቸረር ብር 100.00 የነበውን ብር 160.00፤ ለረዳት ሌክቸረር ብር 65.00 የነበረውን ብር 85.00 በማድረግ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,472,773.20፤
- ለአስተዳደር ሰራተኞች ለሬጅስትራርና አልሙናይ ዳይሬክቶሬት እና ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ብር 97,021.66፤

- በኤክስቴንሽን መርሃ ግብር በመጀመሪያ ድግሪ፣ ለሁለተኛ ድግሪ፣ ትምህርታቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች፣ በተለያዩ ኮሌጆችና የት/ት ክፍሎች ላስተባበሩ ሰራተኞች የፖዚሽን ክፍያ፣ ለት/ት ክፍል ሃላፊዎች ለአስተባባሪዎች የተከፈለ ብር 2,784,095.00 በድምሩ ብር 4,353,889.86 በቦርድ ሳይፈቀድ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል፣

3.2.3. <u>ስጋት</u>፣

የመንግሥት ሀብት እና ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.2.4. <u>*የማሻሻያ ሀሳብ*</u> ፣

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ደንብና መመሪያን በመከተል በሚመለከተው አካል (በቦርድ) እየተፈቀደ ሊወጣ ይገባል፡፡

3.2.5 <u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ*</u>

- *የውስጥ ገቢ መመሪያ ገቢን ለማመንጨት የሚያስፈልግ ወጪ ተሰልቶ በእቅድ ተይዞ በየዓመቱ ለቦርድ በማቅረብ በማጸደቅ መሰራት እንዳለበት ይደነግጋል። እኛም በዚህ መሰረት በየዓመቱ እቅድ ቀርቦ ይፀድቃል። ለብቻው በተለየ መልኩ በዝርዝር ክፍያውን በተመለከተ ቦርድ መወሰን አለበት የሚል በወስጥ ገቢ መመርያ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም ነገር ግን ባለፈዉ ዓመት ኦዲተሮች በሰጡን አስተያየት መሰረት በመጨረሻ በሰኔ 2009 ዓ/ም አጠቃላይ የተከታታይ መመሪያ በሰኔት የቀረበው ዝርዝር ለቦርድ አቅርበን አፀድቀናል።*
- *ለአስተዳደር ሰራተኞች ለሬጅስትራርና አልሙናይ ዳይሬክቶሬት እና ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት የሚከፈለው የትርፍ ሰዓት በቦርድ አልጸደቀም የሚለው በቦርድ ሊጸድቅ አይገባም ምክንያቱ ልክ መምህር አስተምሮ እንደሚከፈለው ይህም ተመሳሳይ ነው ምክንያቱም የተማሪዎች ምዝገባ ቅዳሜና እሁድ ስለሆነ ይህ ቀን ደግሞ የዕረፍት ጊዜ በመሆኑ የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲገቡ ከተደረገ በመንግስት መመሪያ መሰረት መከፈላቸው አግባብ ነው። በማለት ገልፀዋል፡፡*

3.3.1 <u>በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈፀመ ክፍያ፡</u>

3.3.2 <u>ግኝት</u>

ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር፡

- ዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ጽሑፍ ያማከሩበት በሚል በአንድ ተማሪ ብር 5,000፣ ብር 2,000፣ በማድረግ በድምሩ ብር 200,000.00፤
- ለኢንተርናል ኤግዛማይነር (የውስጥ ገምጋሚ) በአንድ ተማሪ ብር 2,500፣ በማድረግ በድምሩ ብር 162,500፤
- ለኤክስተርናል ኤግዛማይነር (የውጭ ገምጋሚ) በአንድ ተማሪ ብር 4,000፣ በማድረግ በድምሩ ብር 184,000.00
- ለቼር ፐርሰን (ሰብሳቢ) በአንድ ተማሪ ብር 200፣ በማድረግ ብር 13,800.00 በኦዲት ናሙና በተመረጡት ብቻ በአጠቃላይ ብር 560,300.00 በመንግስት የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 4 ተመልክቷል፡፡

3.3.3 <u>ስጋት፣</u>

አሰራሩ ወጥነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

3.3.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ የክፍያ ተመን ሊኖረው ይገባል፡፡

3.3.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ከላይ የተገለጹት ክፍያዎች እንደየ ዩኒቨርሲቲው ገቢ መሰረት ተደርጎ በሴኔት ጸድቆ ተግባራዊ የሚደረግ ክፍያ ነው። የተመኑ መነሻ ደግሞ እያንዳንዱ ስራ ስንት ሰዓት ይፈጃል ተብሎ በኮሚቴ ታይቶ ለሰዓት መንግስት ባወጣዉ ተመን መሰረት ተደርጎ ወጥ ሆኖ እንዲሄድ በተከታታይ ትምህርት መመሪያ መሰረት እየተሰራበት ያለ ነው። ስለዚህ ት/ት ሚ/ር ተመን ስላላወጣ የመማር ማስተማር አካል የሆነ

የተከታታይ ት/ት ስራ ሊቆም አይችልም። ለውስጥ ገቢ ስራ ለማመንጨት የሚያስፈልግ ወጪ ገቢን መሰረት ተደርጎ የክፍያ ስርዓት ማውጣት ይችላል።

3.4.1 <u>የጤና ባለሙያዎች የተረኘነት አበል ክፍያን በተመለከተ</u>

3.4.2 <u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፃ 14 ንዑስ አንቀጽ 4፤7 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን፤ ወጪ ከመደረጉ በፊት ሰለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት መመሪያው ላይ በተገለፀው መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል ብር 1,201,184.41፤ በሽሬ ካምፓስ ብር 31,853.03፤ በድምሩ ብር 1,233,037.44 ለጤና ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓት (የተረኘነት) ክፍያ ሲፈፀም የተዘጋጀ የቀን መቆጣጠሪያ ወይም አቴንዳንስ ሳይኖር ክፍያው የተፈፀመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት አልተቻለም፡፡

ዝርዝር በአባሪ ቁጥር 5 ተመልክቷል፤

3.4.3 <u>ስጋት</u>

የተከፈለው ተረኘነት አበል የቀን መቀጣጠሪያ አቴንዳንስ ሳይኖር የተከፈለው የጤና ባለሙያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ለመገኘታቸው አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

3.4.4 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ወጪ እንዳይሆንና ለክትትል እና ለቁጥጥር አመቺ ለማድረግ ትርፍ ሰዓት ለመሰራታቸው ለማረጋገጥ የቀን መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡ ለክፍያ አሰፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም ተጠያቂ ያደርጋል ለወደፊቱም በመመሪያው መሠረት መሠራት ይኖርበታል፡፡

3.4.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለሃኪሞች አቴንዳንስ ማድረግ ይከብዳል ምክንያቱም በባህሪው ሃኪም ሳይገባ ኦን ኮል በሚባል ይከፈለዋል። ከዚህ በተጨማሪ የስራ ባህሪው አስገድዶት ሁልጊዜ በሚቀያየሩበት ጊዜ አጭር የሪፖርትና የርክክብ ስርዓት አላቸው። ከዚህ በላይ እነሱም አቴንዳንስ ለመፈረም ፍቃደኞች አይደሉም። ክሊኒክ ባለሞያዎች ግን አቴንዳንሰ እንድይዙ ለማድረግ እንችላለን።እሰካሁን ያልያዝነዉ ፕሮግራም በስርዓት

ወጥቶ ተግባረዊ ስለሚደረግ እና የሰዉ ህይወት በመሆኑ ማንኛዉመ ባለሞያ የሞያዉ ኢቲክስ መሆኑን ግንዛቤ ቢወሰድ

3.5.1 የውጪ ሀገር መምህራንን የሥራ ግብር በተመለከተ

3.5.2 ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 4 ማንኛውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚገኘው ጠቅላላ የወር ገቢ ላይ በተወሰነው መጣኔ መሠረት ግብር መክፈል እንዳለበት እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም፤ በዩኒቨርሲቲ የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ36 የውጭ ሀገር መምህራን ብር 2,707,460.71 የተከፈላቸው ቢሆንም የሥራ ግብር ብር 882,559.14 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 6 ተመልክቷል፤

3.5.3 ስጋት

በመንግሥት ደንቦች እና መመሪያዎች ተፈጻሚ አለመሆን የመንግስት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም እንድውል መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ መንግሰት በበጀት ዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን ገቢ ያሳጣል፡፡

3.5.4 የማሻሻያ ሀሳብ

በመንግስት ደንብ እና መመሪያ መሠረት የሥራ ግብር መሰብሰብ ወይም ከግብር ነፃ ለመሆናቸው ማስረጃ ሊኖር ይገባል። ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጣውን መመሪያ ማገናዘብ ይገባል፡፡ አላግባብ የሥራ ግብር ሳይቀነስ የተከፈለው ክፍያ የመንግስትን ገቢ የሚሳጣ ስለሆነ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.5.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ብዙ ግንዛቤ ሳይኖረን ልክ እንደ ህንድ መምህራን መስሎን ውል አስረን ስንሰራበት የነበርን ነን። አሁን ግን ውሉ የጊዜ ገደብ ሰጥተን ተማሪዎች በመሃል እንዳይጎዱ ግምት ውስጥ አስገብተን ሰኔ ወር 2009 ዓ/ም እንዲቋረጥ መደረጉን ገልፀዋል።

3.6.1 <u>በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገር ትምህርታቸውን ተከታትለው ያልተመለሱና የውል ግዴታቸውን ያልተወጡ መምህራኖችን ሂሳብ በተመለከተ</u>

3.6.2 <u>ግኝት</u>

ለትምህርት እድል አግኝተው በሀገር ወስጥ እና ከሀገር ወጭ ትምህርት እየተከታተሉ ያሉ መምህራን በስዓቱ ለመመለሳቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና አፈፃፀም በመስከረም/2004 ዓ.ም ላይ በክፍል ሰባት በአንቀጽ 7.2 በንዑስ አንቀጽ 7.1.8 ለለማስተር ድግሪ ከሃያ አራት ወር (2 ዓመት) ለዶክትሬት ድግሪ ከአራት ዓመት መብለጥ እንደሌለበት ቢያመለክትም ከበለጠ ግን እድሉን የሰጠው ተቋም ማረጋገጥ እንዳለበት›› መመሪያው ያመለክታል ይሁን እንጂ፤

- ዩኒቨርሲቲው በሀገር ወስጥ እና ከሀገር ወጭ ትምህርታቸው ለሚከታተሉ ውል ገብተው ለት/ት ወደ ውጪ ሀገር ከተላኩት መምህራን መካከል ለሁለተኛ ዲግሪ 9 ለሦስተኛ ዲግሪ 3 በድምሩ 12 መምህራን ከላይ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሄዱ ሲሆን አካዳሚክ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ሳይቀርብ በበጀት ዓመቱ የተከፈለ ብር 994,941.00 የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ወጪ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 7 ተመልክቷል፡፡

3.6.3 <u>ስጋት</u>

ጊዜያቸውን ጨርሰው የማይመጡ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የተቋሙን እቅድ ለማሳካት እና የመምህርን እጥረት ለመቀነስ ካለማስቻሉም በተጨማሪም መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ መንገድ የሚከፍት አሰራር ነው፡፡ መመሪያውን ያልተከተለ አሰራር ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

3.6.4 የማሻሻያ ሃሳብ

ውጪ አገር እና ሀገር ውስጥ የትምህርት ዕድል አግኝተው ለሚማሩ አካዳሚክ ባለሙያዎች በወቅቱ ያልተመለሱ መምህራን ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ምክንያቱ ተጠቅሶ ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፤

3.6.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ትምህርታቸውን ጨርሰው ያልተመለሱ 90 መምህራን የመረጃ አያያዛችን ችግር ሆኖ በወቅቱ መረጃ ባለመስጠታችን ነዉ። አሁን ግን በዝርዝር ሁሉም ያልጠፉ መሆናቸውና በህጉ መሰረት ያሳደሱ ወይም ጨርሰው ተመልሰው ስራ ገበታቸው ላይ እንዳሉ የሚያሳይ መረጃ አቅርበናል፡፡ በማለት መልሰዋል፡፡

3.6.6 የኦዲተሩ አስተያየት

በምላሹ ላይ 90ዎቹም እንደተመለሱ የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃው ቀርቦ ስለመመለሳቸው የተረጋገጠው የ78 ማስረጃው የቀረበ ሲሆን የ12ቱ የቀረበ መረጃ ባለመኖሩ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.7.1 ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልሆነ የጉዳት ካሳ

3.7.2 ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡በዚህ መሠረት ለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ፡ የህንፃ ስራው ለዘገየበት ከ4 የስራ ተቋራጮች ከሚሰሩት ከ4 ፕሮጀክቶች

ላይ መሰብሰብ የነበረበትና ያልተሰበሰበ ብር 7,347,911.16 ከተለያዩ የእቃ አቅራቢዎች በወቅቱ እቃውን ገቢ ባለማድረጋቸው ብር 138,234.13 በጠቅላላው ብር 7,486,145.29 መክፈል የሚገባቸው የጉዳት ካሳ ያልከፈሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁ.8 ተመልክቷል፡፡

3.7.3 ስጋት

ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥርበታል፡፡

3.7.4 የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲው ከላይ የተመለከተውን ብር 7,538,814.69 ኮንትራክተሮቹ እና አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በገቡት ውል መሠረት አገልግሎቱን ካልሰጡ በመመሪያው መሠረት መክፈል ያለባቸውን የጉዳት ካሳ መክፈል ይኖርባቸዋል።

3.7.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚገኘው የተማሪዎች ዶርሚተሪ ለጉዳት ካሣ የሚሸፍን የክፍያ ሰርተፊኬት የተረጋገጠ በእጃችን ይገኛል፡፡ ስለዚህ በቅርብ ጊዜ ገቢ ይደረጋል፡፡
- የመጋዘን ፣ጋራጅና ላቫጆ እንዲሁም የዲያሪ ፋርምና ሁለት መጋዘኖች በተመለከተ ክፍያ በሚቀርብበት ጊዜ ገቢ ይደረጋል፡፡
- የአስተዳደር ሕንፃን በተመለከተ ግን ሥራው ስለተቋረጠ በውሉ መሠረት ሊሰራልን ስላልቻለ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የጉዳት ካሣ ገቢ እንዲያደርግልን በሕግ ክስ እንዲመሠረት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- በሀገር ደረጃ የተፈጠረው የዶላር ማስተካከያ ዋጋ ለተፈጠረው የዋጋ ንረት ምክንያት የተጓተቱ ብዙ ፕሮጀክቶች በመሆናቸው ይህም በተከታታይ ተፅዕኖ ደርሶበታል ተብሎ የታሰበና እና ካለው የላቦራቶሪ ማቴሪያል እጥረት አንፃር የ2010 የትምህርት ዘመን የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዳይስተጓጎልብን ስለሰጋን ባለው ሁኔታ ፈቅደናል፡፡ ለወደፊቱ አስፈላጊውን ማስተካከያ እናደርጋለን፡፡

3.8.1 <u>በውሉ መሠረት ካላቀረበ አቅራቢ ገቢ ስላልተደረገ ዋስትና በተመለከተ</u>

3.8. 2 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል ሰባት አንቀጽ 30 በንዑስ አንቀጽ 11 በፊደል (መ)፤ (ለ) የመንግሥት መ/ቤት ከአቅራቢዎች እና በውሉ መሠረት የተያዘ ዋስትናዎች፤ ዋራንቲዎች ተገቢውን ክትትል እየተደረገባቸው አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንዲሆን መመሪያው ቢያመለክትም፤

የነጭ ጤፍ አቅራቢ ከሆነ ሮማን ከበደው ከ01/09/2009 ጀምሮ 5000.00 ኩንታል ጤፍ እንዲያቀርብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሠረት ባለማቅረቡ ያስያዙት ዋስትና ብር 1,049,500.00 ተወርሶ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረግ ሲገባው ያልተደረገ እና በቀን 22/03/2010 ዓ.ም ለባንኩ በተፃፈ ደብዳቤ ያስያዙት ቦንድ እንዲታገድላቸው ብቻ የጠየቁ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.10.3 <u>ስጋት</u>

- በውሉ መሠረት አቅራቢው ባለማቅረቡ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ነው፡፡
- አቅራቢው የሚፈለግበትን አገልግሎት ሳይሰጥ በተለያየ ምክንያት ቢያቋርጥ ያሲያዙት ቦንድ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባው አለመደረጉ ለግለስብ ጥቅም እንዲውል መንገድ የሚከፍት አሠራር ነው፡፡

3.8.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ወጪ እንዳይሆንና ለክትትል እና ለቁጥጥር አመቺ ለማድረግ አቅራቢው በውሉ መሠረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ያስያዘው ቦንድ ተወርሶ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲኖርበት ገቢ ያልተደረገበት ምክንያት ተጣርቶ ተገቢውን እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የሚመለከተው የሥራ ክፍል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.8.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

አቅራቢው በጨረታ ወቅት ጤፍ፣ ሩዝ እና ነመን ዘር አሸንፎ ውል አስረዋል። ሩዝ እና ነመን ዘር በአንዴ ስለሚቀርብ ሙሉ በሙሉ በውሉ መሰረት ገቢ አድርገዋል። ጤፍ ውል የታሰረው 5000 ኩ/ል ሲሆን በታዘዘው መሰረት በጊዜው 2900 ኩ/ል ገቢ ካደረገ በኋላ በአጋጣሚ በራሱ ችግር አቅራቢው ታሰረ፡፡ ስለዚህ ዋስትና ወዲያዉ ገቢ የሚሆነው አቅራቢው ምንም ሳያስገባ ሲቀር ነዉ። እንደዚህ አይነት ግማሹ ገቢ ሲያደርጉ ግን በግዥ ህግ መሰረት ቃለጉባኤ ተሰርቶ ጉዳዩ ለግዥ አጽዳቂ ቀርቦ አቅራቢዉ ሳያስገባ የቀረበት ተመርምሮ እና ያደረሰበት ጉዳት መኖሩን አለመኖሩን ታየቶ ሊወረስ ወይም ላይወረስ ይወሰናል ማለት ነው። ስለዚህ እስካሁን የተካሄደው የዋስትናው ጊዜ እንዳያልፈበት ለባንክ ተጽፎ እንዲታገድ ተደርጓል። ሌላው ጉዳዩ በዝርዝር ጽፈን ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ለውሳኔ እንዲቀርብ በሂደት ላይ ነን። በማለት ገልፀዋል፡፡

3.9.1 የእቃና የአገልግሎት ግዥ፣

3.9.2 ግዥን ቆራርጦ መግዛት

3.9.3 ግኝት

ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንጽ 2 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24.12 ላይ ደግሞ ለፕሮፎርማ ግዥ በተፈቀደው አንቀጽ ግዥ ለመፈጸም ሲባል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ

በጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል

- የዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል የመንግስትን ወጪ ሊቀንስ በሚችል መልኩ የግዥ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ አውጥቶ በርካታ ድርጅቶችን በማሳተፍ የመንግስት ጥቅም ማስጠበቅ ሲገባ፣ በናሙና ከተመረጡት

ሰነዶች ውስጥ፣ግዥን በመቆራረጥ የተከናወኑ ክፍያዎች ብር 1,177,071.33 ተፈፀመው ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁ.10 ተመልክቷል፡፡

3.9.4 ስጋት፤

ከተፈቀደው የግዢ ሥርዓት ውጪ ግዢ መፈጸም ግዢዎች ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም እንዳያስገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.9.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- ሆስፒታሉ አዲስ የተከፈተ በመሆኑ እንዲሁም በባህሪዉ ሆስፒታል ጊዜ የማይሰጥ እንደ የውሃ ፓምፓ ጥገና፣ የህመምተኛ ብርድ ልብስ፣ የሀኪሞች ጋዎንና ለሌሎች ለሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች በአስቸኳይ እንዲገዛላቸው ስለሚጠይቁ እና ለመማር ማስተማሩ ሂደትና ለህክምናው አገልግሎት በጣም አስፈላጊዎች ስለሆኑ የተከሰተውን ጊዜያዊ ችግር ለመፍታት በፕሮፎርማ እንዲገዙ ተደርጓል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.10.1 ከጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውጪ በብልጫ የተከፈለ ክፍያ

3.10.2 ግኝት

በጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል

የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ለ2008-2010 የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ለዩኒቨርሲቲው በላከው ውል ላይ የአንዱ Brother Toner TN3320 የንግድ ምልክት ADDIS TONER ሞዴል TN720/TN3330/TN3310/TN3320 ዋጋ ከነቫቱ ብር 661.25 በቪር ጀነራል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ አቅራቢ ጋር ውል ያሰረ ሲሆን፤ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከፈጸማቸው ግዥዎች ውስጥ የተገለጸው Brother Toner TN3320 የንግድ ምልክት ADDIS TONER ሞዴል TN720/TN3330/TN3310/TN3320 በቁጥር 60 ግዥው ሲፈጸም ያንዱ ዋጋ ከነቫቱ ብር 2,050.01 በሆነ ዋጋ ከብሪጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ በዋጋ ማወዳደሪያ ከማእቀፍ ግዥ ስምምነት ውጪ ግዥ በመፈጸሙ

ዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ ብር 83,325.09 (60*2,050.01/123,000.09 — (60*661.25/39,675.00) አለአግባብ በብልጫ እንዲከፍል ተደርጓል።

3.10.3 ስጋት፤

የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፡፡ለምዝበራም መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

3.10.4 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ይህ ሊሆን ያልቻለበት ሁኔታም ተጣርቶ እርምጃ ሊወሰድ እና ለወደፊቱም በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.10.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ለአንድ Brother Tonner TN 3320 ዋጋ ብር 661.25 ሂሳብ ለማቅረብ ቪ.ር ጀኔራል ት/ኃ/ማ/ር ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር የውል ስምምነት ያደረገ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንዲያቀርቡልን በተደጋጋሚ ተጠይቀው ሊያቀርቡልን ባለመቻላቸው በማኔጅመንት ውሳኔ በፕሮፎርማ እንዲገዛ ተደርጓል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.11.1 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ስለተወራረደ ሂሣብ

3.11.2 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች የሚለው ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ እንደሆነ መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በዋናው ግቢ፤

- ከሞኤንኮ (የኢትዮጵያ የሞተርና የመሀንዲስነት ማህበር ሊሚትድ አ.ማ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ለተገዛበት ብር 612,831.88፤ ሲከፈል መቅረብ ያለበት

የሽያጭ ደረሰኝ (cash sale invoice) መሆን ሲገባው፣ ሂሳቡ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (Cerdit sale invoice) ተወራርዶ ተገኝቷል፡

3.11.3 ስጋት

ሂሣቡ ሁለት ጊዜ ሊመዘገብ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው በእዳ ሊጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡

3.11.4 የማሻሻያ ሀሳብ

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ክፍያ ሲከናወን ለግዥም ሆነ ለአገልግሎት ለተከፈለበት ሂሳብ ሲወራረድ የሽያጭ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.11.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሞኤንኮ ግን ከካምፓኒዉ በማሰመጣት እናያየዘዋለን። በማለት ገልፀዋል፡፡

3.12.1 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ለዮሐንስ ዓባይ ኮንሰልቲንግ ኮንስትራሽንና ኢንጂነሪንግ ለአማካሪነት እና ሱፐርቫይዘርነት ክፍያ በ2008 በጀት ዓመት መከፈል የሚገባው ብር 638,250.00 በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ መገኘቱ ታውቋል፡፡

3.12.2 ስጋት

ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ በፈፀመበት እና አቅርቦቱን ባገኘበት በጀት ዓመት ሂሳቡ በወጪ ባለመመዝገቡ የበጀት አጠቃቀሙን የተዛባ ያደርገዋል፤

3.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል ፡፡

3.12.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ለዮሐንስ ዓባይ ኮንሰልቲንግ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ለአማካሪነት እና ሱፐርቫይዘርነት ክፍያ በ2008 በጀት ዓመት መከፈል የሚገባውን በተመለከተ ተቀብለናል እናስተካክላለን የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

3.13.1 <u>ለክፍያው ማረጋገጫ ያልቀረበለት ሂሣብ፤</u>

3.13.2 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት፡- ክፍያዎች ሲፈፀሙ ውል የተገባላቸው ሥራዎች መጠናቀቃቸውና የእቃዎች ርክክብ መፈፀሙን፤ አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ እንደሚገባ፤ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/2 ፊደል ለ መሰረት፤ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት መመሪያው ቢያመለክትም፡፡

- በተቋሙ የኤሌክትሪክ ኃይል ግምት EEU-NORTHEN REGIONን 796.4 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ሥራን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የግምት ሂሳብ ብር 1,804,956.36 እንደሆነና የዋጋ ልዩነት ቢከሰት ልዩነቱን ተቋሙ እንደሚከፍል ተገልፆ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን የመስመር ዝርጋታው ስለመጠናቀቁ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብና አገልግሎቱ ሳይገኝ ሂሳቡ በወጪነት መመዝገቡ፤

3.13.3 <u>ስጋት</u>

የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.13.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ክፍያዎች ከመከናወናቸው በፊት ሥራዎች መጠናቀቃቸውና የእቃዎች ርክክብ መፈፀሙን እንዲሁም አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ

ይገባል፡፡ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት የሚመለከተው የሥራ ክፍል ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

3.13.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ክፍያው ለመንግስት መስሪያ ቤት የተፈጸመ በመሆኑ በሚል ነው ሂሳቡን ያስተላለፍነው ለቀጣይ እናስተካክለዋለን የተማሪዎች ግን ለአራት ወራት አፓረንት ሽፕ ወጥተው በበጀት ዓመቱ ስለማይመለሱ ነው ሂሳቡ የተላለፈው። በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.14.1 <u>የሕንጻና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተመለከተ</u>

3.14.2 <u>የተቋረጠ የግንባታ ሥራ በተመለከተ</u>

3.14.3 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል ሰባት አንቀጽ 30 በንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል (መ) የመንግሥት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን እና የመንግሥት መ/ቤቱን ጥቅም መከበራቸውን እና የመንግሥት መ/ቤቱ ግዴታዎችን የተፈፀሙ መሆኑን መረጋገጥ እንደሚገባቸው በተደነገገው መሠረት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡- በዋናው ግቢ ቴዎድሮስ አበራ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር ለአስተዳደር ሕንፃ /Administration office building (Lot 24) ለማሰራት በዋናው ውል ብር 88,482,547.44 ለተለዋጭ ሥራ /variation Order/ ብር 1,134,144.46 በድምሩ በብር 89,616,691.90 ለመስራት ተዋውሎ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 22,602,258.11 የተከፈለው ሲሆን ከተቋሙ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተረጋግጦ በተሰጠን ማስረጃ ሥራው የደረሰበት ደረጃ 28.07% መሆኑና ከቀን 01/03/09 ዓ.ም ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር AKU/VPASA 4483/01/09 የሥራ ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን ያቋረጠ ቢሆንም በውሉ መሠረት በሕግ የተጠየቀበት እና ውሳኔ የተገኘበት ማስረጃ የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንፃር በሥራ ተቋራጩ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.14.4 ስጋት

በመንግሥት ታምኖባቸው የውጡ ሕጎች፣ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የመንግሥት ሀብትና ንብረት ያለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

3.14.5 የማሻሻያ ሀሳብ

በውል የተገቡ ግዴታዎችን ተፈፃሚ ማድረግ ይገባል፡፡

የመ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ በሕግ የተቋሙ ጥቅም እንዲከበርለት ማድረግ ይገባል፡፡

3.14.6 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ኮንትራክተሩ በውሉ መሰረት መፈጸም ሲያቅተው ከአማካሪ መሀንዲስ ጋር በመሆን ውሉ እንዲቋረጥ አድርገነል። በተጨማሪ የህግ ክፍላችን የዩኒቨርስትያችን ጥቅም ለማስከበር ከአማካሪ መሃንዲስ ጋር በመሆን በእንቅስቃሴ ላይ ናቸው። በተጨማሪ ዋስትና ለሆነው ባንክ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግልን ደብዳቤ ጽፈናል። እነሱም ዩኒቨርሲቲ ድረስ በመምጣት ሁኔታውን እያጤኑት ነው። ዝም አላልንም እየሰራን ነን። በማለት ገልፀዋል፡፡

3.15.1 የግንባታዎች አገልግሎት አሰጣጥ

3.15.2 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል አራት አንቀጽ 16 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 በፊደል (ሀ) በአቅራቢው እና በመንግሥት መ/ቤቱ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልፅ ማመልከት እንዳለበት በተደነገገው መሠረት በውሉ የሚቀርበው ዕቃ፤ የግንባታ ዘርፍ ሥራ፤ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ዓይነት እና ጥራት፤ የማስረከቢያ ጊዜውን እና የክፍያ ጊዜውን የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ማስረከብ ባለባቸው ጊዜ ማስረከባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በዋናው ግቢ ለዘርፈ ብዙ አገልግሎት እንዲውሉ ታስበው የተገነቡ ግንባታዎች ተጠናቀው ርክክብ ቢፈፀምም ከፍተኛ ገንዘብ የወጣባቸው ግንባታዎች በሚፈለገው መጠን ግልጋሎት አለመስጠታቸውን በኦዲት ቅኝትና ዳሰሳ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በ2009 በጀት ዓመት ርክክብ ተፈጽሞባቸው በከፊል አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ በ2 ሎት የተከፈሉ ጠቅላላ ዋጋ በድምሩ ብር 352,703,934.88 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 345,258,961.91 ወጪ የተደረገባቸው ሕንፃዎች ሙሉ የሆነ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

ተራ ቁጥር	የፕሮጀክቱ ስም	ርክክብ የተፈፀመበት ቀን	ሕንፃው የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል	ሕንፃው ተገንብቶ አገልግሎት የማይሰጡ ክፍሎች	የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ/ወጪ/	ለሕንፃ ሥራ ተቋራጩ የተከፈለው
1	MULTI PURPOSE AUDITORIUM BUILDING.LOT-23	18/08/09	የመሰብሰቢያ አዳራሽ/MAINHALL& MINI HALL -የእንግዳ ማረፊያ	ካፌ፣ኪቺን እና ሌሎች CONTROL ROOM.	305,637,136.16	304,663,211.01
2	CONSRUCTION OF DORMITORY &REGISTRAR.LOT 31	21/11/08	የተማሪዎች መኖሪያ፣መጋዘን	ሪጂትስራር፣እና ሌሎች የስራ ክፍሎች/MAIN CAFTERIA,SOCIAL CAFÉ.	47,066,798.72	40,595,750.90
				ድምሩ	**352,703,934.88**	**345,258,961.91**

ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

3.15.3 <u>ስጋት</u>

ውስን የመንግሥት ሀብትና ንብረት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

3.15.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የመንግስት ሀብትና ንብረት ደንብና መመሪያ መሰረት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚሰጥ ሁኔታ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.15.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በዋናነት የመሰብሰቢያ አዳራሹ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ የአዳራሹ ካፌ ግን መሟላት የሚገባቸው ቁሳቁሶች አሟልተን ለስታፍ ላውንጅና ለተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲውል ይደረጋል፡፡

- ዶርሚተሪ፤ መጋዘን እና ሪጂስትራር ሎት 31 ፕሮጀክቶች በተመለከተ አብዛኛውን ማለት ዶርሚተሪ እና መጋዘን አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የሬጂስትራር ሕንፃ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ጀምሯል። የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

3.16.1 ባልተሟላ ማስረጃ ያለ አግባብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣

3.16.2 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የክፍያ መመሪያ ቁጥር4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (4) (7) (8)

- ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን
- ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡንና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀዱን
- ለኮንስትራክሽን ወጪዎች የክፍያ ምስክር ወረቀት መቅረቡን እና በትክክል መሰላቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ተቋሙ ከኢ.ፌዴሪ ት/ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር 7/-259/1715//09 በቀን17/02/09 በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተባባሪነት የዩኒቨርሲቲዎችን ኔትወርክ ዝርጋታ የሁሉንም ተቋማት ፍላጎት አቀናጅቶ ለመስራት ለሁሉም ፕሮጀክቶች መሣሪያዎች ከውጪ የሚመጡ መሆናቸውን በመጥቀስ የተቋሙን ድርሻ ወደ ት/ሚ/ የባንክ ሂሳብ እንዲያስተላልፍ የገለፀ ቢሆንም ፤መሣሪያዎች ግዥ ተፈፅሞ ስለመግባታቸው እና ርክክብ ስለመፈፀሙ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀረጥላቸው፤ የመሠረተ-ልማት የኔትወርክ ዝርጋታው በአግባቡ ስለመፈፀሙ የግንባታ የክፍያ ምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲስ ሳይፀድቅ እና አገልግሎት መስጠቱ ሳይረጋገጥ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 468205 በቀን 30/10/09 ብር 51,000,000.00 ክፍያው ተፈፅሞ እና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

3.16.3 ስጋት

- ውስን የመንግሥት ሀብትና ንብረት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- ንብረቱ ወደ ለዩኒቨርሲቲ ገቢ ላይሆን ይችላል፡፡
- የመሠረተ ልማት ዝርጋታው በአግባቡ ላይከናወን ይችላል፡፡
- በተጨማሪም የሂሳብ ሪፖርቱንም የተዛባ ያደርገዋል፡

3.16.4 የማሻሻያ ሀሳብ

- የመንግስት ሀብትና ንብረት በደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ማስረጃዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡
- አገልግሎቱ ከመገኘቱ በፊት እና ንብረት ገቢ ከመደረጉ በፊት የሚፈፀሙ ክፍያዎችን የተሟላ ማስረጃ እስከሚቀርብላቸው ድረስ በቅድመ-ክፍያ ሂሳብ መያዝ ይገባል፡፡

3.16.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ይህ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ በት/ሚ/ር አስተባባሪነት የሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በአንድ ማዕቀፍ ተገዝቶ የሚተከል ስለሆነ ለብቻችን የሚሰጥ ዶክመንት (ማስረጃ) የለም፡፡ ገንዘቡ ከመንግሥት መ/ቤት ወደ ሌላ መንግሥት መ/ቤት የተላለፈ ነው፡፡ ብክነት አይኖርም ለግለሰብ አልተላከም ወደ ግዥ ኤጀንሲ የተላለፈው ደብዳቤ አያይዘናል፡፡ የሂሳብ መደቡ ት/ሚ/ር በፃፈው ደብዳቤ መሠረት ተደርጎ የተካሄደ ምዝገባ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

3.16.6 የኦዲተር አስተያየት

ከኢ.ፌዴሪ ት/ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር 7/-259/1715//09 በቀን17/02/09 በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተቋሙ የሚደርሰውን ድርሻ ለኔት ወርክ ዝርጋታ እና ለመሣሪያ ግዥ በ6324 ሂሳብ መደብ ተይዞ በባንክ እንዲተላለፍ መመሪያ አስተላልፏል፡፡ ነገር ግን ከ8 ወር በኃላ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 468205 በቀን 30/10/09 አገልግሎቱ ከመገኘቱ በፊት በቅድመ-ክፍያ ሂሳብ መያዝ የሚገባውን ሂሳብ ፣በችሮታ ጊዜ ክፍያ 6324 በዴቢት 5001 በክሬዲት በማሳየት የተከፈለ ሲሆን በሐምሌ 2009 5001 ን ዴቢት 4103 ን ክሬዲት በማድረግ ወጪው በ2009 የበጀት ዓመት መሣሪያዎች ተገዝተው ገቢ ሳይደረጉ፣ /የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሣይቀረጥላቸው፣ የኔትወርክ ዝርጋታ ሳይዘረጋና /አገልግሎቱ /ሳይገኝ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ መገኘቱ አግባብ ሆኖ መገኘቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ሂሳቡን በተሰብሳቢ በመያዝና ተገቢ የሆነ ደጋፊ መረጃዎች ሲቀርቡ በወጪ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

4. የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

4.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና የዩኒቨርሰቲው የተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት እንዲወራረዱ የሚደረግ መሆኑ ሲጣራ፣

ከመደበኛ በጀት

- በሂሣብ መደብ 4203 ለ99 ግለሰቦች በቅድሚያ የተከፈለ ብር 730,447.75 ሂሳቡ ሳይወራረድ ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ድረስ የቆየ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ በዚሁ ሂሳብ መደብ ለ5 ግለሰቦች እና ድርጅቶች በቅድሚያ የተከፈለ ብር 45,990.00 ሂሳቡ ሳይወራረድ ከ4 ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ፤ በድምሩ ብር 776,437.75 መኖሩ፤
- በሂሣብ መደብ 4251 በተቋሙ ዋናው ግቢ ቴዎድሮስ አበራ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር ለአስተዳደር ሕንፃ /Administration office building (Lot 24) ለማሰራት ተዋውሎ በቅድመ ክፍያ የተከፈለ ቢሆንም የሕንፃ ሥራው ተቋርጦ የሚገኝ እና በህንፃ ተቋራጩ ስም የሚገኝ በወቅቱ ያልተወራረደ እና ከ1 ዓመት ከ4ወር በላይ የቆየ ብር 19,946,833.32 የሚገኝ መሆኑ፤
- በ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት (ከ30/07/2007 እስከ 30/5/2009) ባለው ጊዜ ውስጥ ጂ .አይ .ዜድ.አይ.ኤስ /GIZI-IS/ ራሱ እና ከሌሎች 3 የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ጋር በመሆን ለአቅራቢዎች በሚሰጥ የቅድመ-ክፍያ ብር-10,097,839.44 ከ10 ወር እስከ 2-ዓመት ከ9 ወር የቆየ ሂሳብ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በጠቅላለው ብር 50,970,328.30 ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ የቆየ የተሰብሳቢ ሂሣብ መኖሩ ታውቋል፡፡

4.1.2 ስጋት

- የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲፈጠር ሊያደርግና ሂሳቡ ሊሰበሰብ ወደ ማይችልበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡
- በመንግሥት ታምኖባቸው የወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የቅድመ ክፍያ ሂሳቦች ገንዘብ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲወራረዱ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በ 4203 ከታየዉ ያልተወራረደ ሂሳብ የ 113 ብር 870486.82 ተመላሽ ተደርገዋል።
- በ4251 የቴዎድሮስ አበራ ለንብ ኢንተርናሽናል ባንክ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ ደብዳቤ ጽፈናል።
- በ4253 የታየ ያልተወራረደ ሂሳብ 20 ሚልዮኑ ከመንግስት የህክምና መሳርያ እንዲገዛ የተከፈለ ሁኖ መሳርያዎቹ ከዉጭ አገር ስለሚመጡ መሆኑን ግንዛቤ ቢወሰድ
- የGIZI-IS እና ሲግማ ሰነዶች ተልከው በ2010 በጀት ዓመት ተወራረደዋል፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

5. የተከፋይ ሂሣብ

5.1.1 በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብን በተመለከተ፣

5.1.2 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ከመደበኛ ብር 5,485,644.85 ከ4 ወር እስከ 5 ዓመት ከ4 ወር ከውስጥ ገቢ ደግሞ ብር 2,347,612.12 ፤ በድምሩ ብር 7,833,256.97 በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 11 ተመልክቷል

5.1.3 ስጋት

ግዴታ የተገባባቸው ሂሳቦች በወቅቱ ማወራረድ ካልተቻለ ተጨማሪ ወጪን ሊያስከትልና ለቅጣትም ሊዳርግ ይችላል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ግዴታ የተገባበቸው ሂሳቦች ገንዘብ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲወራረዱየእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በ5002 ሂሳብ መደብ የሚታየው የ 11 ሰዉ ብር 317543.48 ተከፍለዋል፡፡ ቀሪው የፕሮጀክት ስለሆነ ቀጣይ ነው አይወራረድም ፡፡
- በ5061 ሂሳብ መደብ የመያዣ ሂሳብ የጠየቀ ስለሌለ አልከፈልንም ፡፡ ኮንትራክተሮች እንዲወስዱት ማስታወቅያ እናወጣለን ካልሆነ ገቢ መሆን የሚችል ከሆነ ወደ መንግሥት ገቢ እናድርገዋለን፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

6. ንብረት፣

6.1.1 አላቂና ቋሚ እቃዎች፣

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በሽሬ ካምፓስ

የንብረት ክምችትን በተመለከተ

- በንብረት ክፍል ከ1 ዓመት በፊት ተገዝተው ያለአገልግሎት የተለያዩ ብረት ድስቶች የተለያየ መጠን እና ይዘት ያላቸው፤ white board ተከማችተው ያሉ መሆኑ፤
- የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ከሌሎች ቋሚና አላቂ ንብረቶች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- ብዛት ያላቸው የኮምፒውተር ወረቀቶች፤
- ብዛት ያላቸው ፍሊቶች ከ1 ዓመት በላይ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

<u>ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች</u>

- ብዛት ያላቸው ማይክሮስኮፖች /የላቦራቶሪ ዕቃዎች/
- ዴል ላፕቶፖች
- ለሥነ ምድር ጥናት የሚያገለግል መሣሪያ እና ፍሪጆች፤ የሸንኩርት መፍጫ፤ የምግብ ማብሰያ ማሽኖች ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች ያለአገልግሎት ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡

6.1.2 ስጋት

ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ንብረቶቹ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይገባል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በኦዲት ወቅት በተሰጠን አስተያየት መሰረት ሁሉም ተስተካክለዋል። በማለት ገልፀዋል፡፡

6.2.1 በዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ውስጥ ስለአልተካተቱ ንብረቶች በተመለከተ፤

6.2.2 ግኝት፤

- በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2፤ እንዲሁም በክፍል 2 አንቀጽ 7 ን.አ.1.ረ በ□□መቱ □ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ በማድረግ የቋሚ ንብረቶቹ ያሉበት አቋም □□ም □ሚኖኙበት ቦታላ□ ማናቸውም ለውጥ ቢኖር ይኸው በቋሚ ንብረት ካርዱ ላይ በቋሚ ንብረት መዝገብና በጠባቂዎች የንብረት ወይም የመጋዘን ኃላፊ □ር□ር □ቱስዓ □እንዲመለከት መደረግ እንዳለበት መመሪያው በሚያመለክተው መሠረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤
- የቤተ-መጽሐፍት ንብረት ቆጠራ እና የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች በዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ውስጥ እንዳልተካተቱ፤

- በጤና ሳይንስና ሪፈራል ሆስፒታል በተካሄደው የንብረት ቆጠራ በሰራተኞች እጅ የሚገኙ 13 ላፕቶፖች በሰኔ 30/2009 በቆጠራ ያልተካተቱ መሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

6.2.3 ስጋት

የንብረት ጥፋት እና ጉድለት ቢኖር ማወቅ አያስችልም፡፡

6.2.4 የማሻሻያ ሀሳብ

ቋሚ እና አላቂ ንብረቶችን በሙሉ ቆጠራ ማከናወን ይገባል፡፡

6.2.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ለሚቀጥለው አስፈላጊውን በማድረግ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ እንዲደረጉ ይደረጋል፡፡
- የቤተ -መጻሕፍት ቆጠራ ተካሂዷል፡፡ ቢሆንም ግን የመጻሕፍት ቆጠራ ለብቻው ስላልተካሄደ መርሐ-ግብር ወጥቶለት ይካሄዳል፡፡ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ በዋናው ስቶር የነበረ ተቆጥሯል፡፡ ነገር ግን ከዋናው ስቶር በሞዴል 20 ወጪ የተደረጉ ንብረቶች ሥራ ላይ ይውላሉ በሚል አስተሳሰብ አልተቆጠሩም፡፡ ይህንን በቀጣዩ እናስተካክላለን በማለት ገልፀዋል፡፡

7. ልዩ ልዩ

7.1.1 የፍትሐ-ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ

7.1.2 ግኝት

ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢው ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

8. የውል ግዴታቸውን ያልተወጡ

- የውል ግዴታቸውን ባልተወጡና ክስ ከተመሰረተባቸው ብር 1,115,633.87 የገንዘብ መጠን የያዙ 16 ጉዳዮች እስካሁን ገንዘቡ ከባለጉዳዮቹ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

8.1.1 ላፕቶፕና አድቫንስ ያልመለሱ

- ላፕቶፕና አድቫንስ ባልመለሱና ክስ ከተመሰረተባቸው ብር 79,373.30 የገንዘብ መጠን የያዙ 5 ጉዳዮች እስካሁን ገንዘቡ ከባለጉዳዮቹ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ውስጥ ብር 8,200.00 ቪዲዮ ካሜራ ያልመለሰና በክርክር ሂደት ያለ መሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.1.2 ለህግ ክፍል ተመርተው ክስ ያልተመሰረተባቸው ጉዳዮች

- የውል ግዴታቸውን ባልተወጡ ላይ በህግ ክፍል ክስ መመስረት ሲገባው ያልተመሰረተባቸው 8 ባለጉዳዮች የሚፈለግ ብር 354,628.22 በኦዲት ወቅት የተገኘ መሆኑ፤

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 12 ተመልክቷል

8.1.3 ስጋት፣

- በባለዕዳዎች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ የመንግሥት ገንዘብና ንብረት ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲውል ዕድል የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ገንዘቡ እና ንብረቱ ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊያደርስና ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲከሰት መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

8.1.4 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

ተቋሙ በወቅቱ ክስ ያልተመሰረተባቸው ባለጉዳዬች ላይ ጥቅም ከማስከበር አንጻር ህጋዊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የተወሰኑት በውሳኔው መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የሚመለከተው የስራ ክፍል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8.1.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

አንድ ላፕቶፕ ተመልሰዋል።የተቀሩት ጉዳዮች ህግ ፊት ቀርበዋል በአፈጻጸም ሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

9. በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ እርምጃ አለመወሰዱን በተመለከተ

9.1.1 የወጪ ሂሳብ

9.1.2 <u>ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች</u>

- የትርፍ ሰአት ላስተማሩ መምህራን፣ ከመሰናዶ ት/ቤቶች የተውጣጡ ተማሪዎችን (out Reach) ላስተማሩ የተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን እና የክረምት ትምህርት ላስተማሩ መምህራን በክሬዲት አወር (credit hours) እንዲከፈል ከተፈቀደው መጠን በላይ በድምሩ ብር 1,198,264.48 ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለ፣
- ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በአይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ብር 31,200.00 በቀጥታ እና ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ኪራይ ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ ብር 262,275.00፣ በድምሩ ብር 293,475.00 በዓይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ያለአግባብ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ ይህ ግኝት በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት አስተ በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ሳይወሰን ወይም ሌላ በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር የተፈፀመ፤
- በዩኒቨርሲቲው ማናጅሜንት ካውንስል በተወሰነው መሠረት ከባንክ ወጪ ሆኖ ብር 5,269,247.42 ለተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ሞጁል ላዘጋጁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ፣ ፈተና ለፈተኑ እና ላማከሩ በሚል በድምሩ ብር 696,583.32 የተከፈለ መሆኑ ፣

የመጀመሪያ እና የ2ኛ ዲግሪ፣ የክረምት ት/ት እንዲሁም የኤክስቴሽን ት/ት ላስተባበሩበት የፖዚሽን /Overload/ ክፍያ በሚል ለተለያዩ የአስተዳደርና የአካደሚክ ሠራተኞች ብር 2,115,860.00 የተከፈለ፣በድምሩ ብር 8,081,690.74 በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ መወሰን ያለበት ክፍያ ሳይወሰን ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንምበ2009 በጀት ዓመትም በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

9.1.3 <u>የዕቃና የአገልግሎት ግዥ፣</u>

- ብር 906,468.95 በተራ ፋክቱር ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡-

- ብር 324,962.22 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ሂሳቡ ተወራርዶ መገኘቱ፡-
- ብር 187,484.07 ገንዘቡ መከፈሉን የሚያረጋግጥ የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (credit sales invoice) ብቻ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፡-
- ብር 18,440,235.40 ከገቡበት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች መሰብሰብ የነበረበት የጉዳት ካሳ አለመሰብሰቡ፣
- ከ2008-2010 የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ለዩኒቨርሲቲው በላከው ውል ላይ የአንድ UPS 1500VA የንግድ ምልክት BPC ሞዴል Powergempro1500ES ዋጋ ከነቫቱ ብር 10,079.75 መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ግዥ ሲፈጸም ያንዱ ዋጋ ብር 12,989.25 በሆነ ዋጋ በመገዛቱበድምሩብር 203,665.00 (/70*12,989.25/-/70*10,079.75/) ለአቅራቢ ድርጅቱ በብልጫ መከፈሉ፣እና ተመላሽ አለመደረጉ፤-

ነዳጅን በተመለከተ

- ስለዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ አጠቃቀምም ሆነ በዩኒቨርሲቲው ሥር ስላሉት ተሽከርካሪዎች መረጃ በመመሪያው በተቀመጠው መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፣
- በዋና ግቢ፤ በሪፌራል ሆስፒታል እና በሽሬ ካምፓስ የሚገኙ፣ ባጠቃላይ የ3 ጀኔሬተሮች የነዳጅ ፍጆታ ሲዳሰስ ለጀኔሬተሮቹ የዋለውን የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ መሆኑ፣

በ2007 በጀት አመት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

- የትርፍ ሰአት ላስተማሩት የህክምና ዘርፍ ረዳት ፕሮፌሰሮች በክሬዲት አወር (credit hours) ብር 120.00 መከፈል ሲገባ ብር 400.00 በመከፈሉ ከተፈቀደው መጠን በላይ በድምሩ ብር 77,840.00 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
- በዩኒቨርሲቲው የመንግስት የጋራ መኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በየደረጃው ከሚገባቸው የቤት አበል ላይ ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ ብር 138,205.00 በዓይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ያለአግባብ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ፣

- በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የተደረገ በቁጥር አንድ ሳውንድ ፕሩፍ ጀኔሬተር ብር 4,499,700.00 የተከፈለበት ቢሆንም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች እንደገና በረጋገጡት መሰረት ዕቃው በውሉ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (specification) መሰረት አለመሆኑ ስለተረጋገጠ ዩኒቨርስቲው ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ በ2007 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት ባሉት የበጀት ዓመታት ርክክብ የተፈፀመባቸው ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- ግንባታዎችን ውል ከገቡበት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች መሰብሰብ የነበረበት ብር 21,163,962.31 የጉዳት ካሳ አለመሰብሰቡ፣
- በፕሣ 9 የሥራ ደረጃዎች ላይ ያለውድድር እና የሥራ ልምዳቸው አግባብነት ሳይኖረው በመማር ማስተማር ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በአይ ቲ ዳይሬክተርነት እና በተቋማዊ ዕቅድና አፈፃፀም ግምገማ ማዕከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት መመደባቸው፣
- በዋናው ግቢ ቤተ-መጽሐፍት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ እንዲሁም የተገነጣጠሉና ተገቢውን ጥገና ያላገኙ የተለያዩ መጻህፍት መኖራቸው፣ በተጨማሪም በስጦታ የተገኙ ነገር ግን ዋጋቸው ያልተገለጸ የተለያዩ መጽሐፍት መኖራቸው፣

9.1.4 <u>ስጋት፣</u>

ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ተቋሙ በኦዲት ሪፖርት ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አብዛኞቹ ተግባራዊ አለማድረጉ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፍት አሠራር ሲሆን፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

9.1.5 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የአሠራር ግድፈቶቹ ለገንዘብና ንብረት መጥፋትና መጉደል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አሠራሮች በመሆናቸው በጉዳዮቹ ላይ ተቋሙ እርምጃ እንዲወስድ በድጋሚ እሳስባለን፡፡

9.1.6 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- አብዛኛው ከዚሁ ከውስጥ ገቢ ጋር ተያይዞ በ2008 ዓ/ም የታዩ ስለሆኑ መልሱ በዚሁ ቢታይ።
- ሳውንድ ፕሩፍ ጀነረተር በህግ ሂደት ላይ ነዉ።
- የህንጻዎች ምዝገባ እስካሁን መረጃ ለማግኘት ሞክረን አልተቻለም አሁንም በማፈላለግ ሂደት ላይ ነን።
- የፐሳ 9 የተቋማዊ ዕቅድ ተስተካክለዋል።የአይሲቲ ማስታወቅያ ወጥቶ ባለሞያ ሊገኝ አልተቻለም።
- አጠቃላይ ለሌሉ የተከፈለ ከ 13 ሺ ብር በላይ ነዉ።ሁሉም እንዲመለስ ተደርገዋል።ይህ ብር 4,571.60 በኦዲት ወቅት ሳምፕል የዋለ በመሆኑ ነዉ በተመላሽ ብር ዉስጥ የተካተተ ነዉ ተመልሰዋል።
- የመጻህፍት በሂደት ላይ ነን። በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!